# ይድረስ ለአባ

# "ጳውሎስ ቄሳር"

*ወፈርዖን፣ ወናቡከደነፆር፣ ወሔሮድስ*

## "እንግዲህ በነቢዩ በዳንኤል የተባለውን የጥፋትን ርኩሰት በተቀደሰችው ሥፍራ ቆሞ ስታዩ፥ አንባቢው ያስተውል" ማቴ፤ 24፡ 15


ቄሳር የሚለው ስም በጥንታዊት ሮም የሚነግሡ ነገሥታት የሚጠቀሙበት፣ ከመጠሪያ ስማቸው ፊት የሚነገር ወይም የሚጻፍ ቅጽል (የማዕረግ) ስም ነው። እንደየሀገሩ ልማድና ባህል ነገሥታቱ ቅጽል ወይም የማዕረግ ስም አላቸው። ለምሳሌ ጥንታውያን የግብጽ ነገሥታት ፈርዖን፣ ጥንታውያን የእስራኤል ነገሥታት ሔሮድስ፣ የፋርስና የባቢሎን ነገሥታት ደግሞ ናቡከደነፆር በሚለው የወል ስም ይጠሩ እንደነበረው ማለት ነው።

ከላይ የጠቀስናቸው ጥንታውያን ነገሥታት ሁሉ በአብዛኛው በጭካኔና በአምልኮ ጣዖት ይታወቃሉ። በተለይም የሮማ ቄሳሮችን ከሌሎቹ ለየት የሚያደርጋቸው ነገር ቢኖር ሌሎቹ ነገሥታት የሚፈጽሙትን ግፍ በሙሉ ከመፈጸማቸው አልፈው ተርፈው የራሳቸውን ምስል (ቅርጽ) አስጠርበው፣ በዋና ዋና አደባባይ ላይ አስቁመው እንዲመለኩ ማድረጋቸው ነው።

ፈርዖኖች የአገዛዝ ቀንበር በማክበድ ፣ ሕጻናትን በጭካኔ በመግደል፣ ኃይለኛ የጉልበት ሥራ በማሠራት በተለይም በእስራኤላውያን ላይ እጅግ በታም አሰቃቂ ግፍ ፈጽመውባቸዋል። "ግብፃውያንም የእስራኤልን ልጆች በመከራ ገዙአቸው። በጭቃ ሥራ፥ በጡብም በእርሻም ሥራ ሁሉ፥ በመከራም በሚያሠሩአቸው ሥራ ሁሉ፥ ሕይወታቸውን ያስመርሩአቸው ነበር" (ዘጸ፤1፡13-14)። በተጨማሪም ጣዖታትን አስቀርጸው ሲያመልኩና ሲያስመልኩ ነበር እንጂ የራሳቸውን መልክ አስጠርበው አምልኩን እስከማለት አልደረሱም።

የፋርስና የባቢሎን ናቡከደነፆሮች 6 በ 60 ክንድ የሆነ የወርቅ ጣዖት በአደባባይ አቁመው አመለኩ፣ አስመለኩ፣ "ለዚህ ያልሰገደ ይቀጣል" እያሉ ሲያስፈሩሩ ይቆዩ እንጂ ምስላችን ተቀርጾ እንመለክ አላሉም። ያም ሆኖ በዳንኤልና በሠለስቱ ደቂቅ አምላክ በልዑል እግዚአብሔር ኃይል፣ በሊቀ መላእክት በቅዱስ ገብርኤል ተአምር አምልኮ ጣዖቱን ትተው ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ተመልሰዋል። ለምሳሌም ሦስተኛው ናቡከደነጾር "ናቡከደነፆርም መልሶ መልአኩን የላከ፥ ከአምላካቸውም በቀር ማንም አምላክ እንዳያመልኩ ለእርሱም እንዳይሰግዱ ሰውነታቸውን አሳልፈው የሰጡትን የንጉሡንም ቃል የተላለፉትን በእርሱ የታመኑትን ባሪያዎቹን ያዳነ፥ የሲድራቅና የሚሳቅ የአብደናጎም አምላክ ይባረክ" (ዳን፤ 3፡ 28) ብሎ ከጥፋቱ ሁሉ ተመልሷል። አራተኛ ናቡከደነጾር ደግሞ በትዕቢት ምክንያት ከሰውነት ጉዳና ወጥቶ በተፈጥሮ እንስሳ ወደ መሆን ተለውጦ ሰባት ዓመት ሙሉ እንደ በሬ ሳር ከበላ በኋላ ንስሐ ገብቶ "አሁንም እኔ ናቡከደነፆር የሰማይን ንጉሥ አመሰግናለሁ፥ ታላቅም አደርገዋለሁ፥ አከብረውማለሁ። ሥራው ሁሉ እውነት፥ መንገዱም ፍርድ ነውና፥ በትዕቢትም የሚሄዱትን ያዋርድ ዘንድ ይችላልና" (ዳን፤ 4፡ 37) በማለት መመለሱን ነቢዩ ዳንኤል ይመሰክራል።

ሔሮድሶቹም ለሥልጣናቸው ሲሉ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሕጻናትን በማሳረድ ቤተልሔምን በደም ጉርፍ እንድትጥለቀለቅ ያደረጉ ግፈኞች ናቸው። "ከዚህ በኋላ ሄሮድስ ሰብአ ሰገል እንደ ተሣለቁበት ባየ ጊዜ እጅግ ተቆጣና ልኮ ከሰብአ ሰገል እንደ ተረዳው ዘመን በቤተ ልሔምና በአውራጃዋ የነበሩትን፥ ሁለት ዓመት የሆናቸውን ከዚያም የሚያንሱትን ሕፃናት ሁሉ አስገደለ። ያን ጊዜ በነቢዩ በኤርምያስ፥ ድምፅ በራማ ተሰማ፥ ልቅሶና ብዙ ዋይታ፤ ራሔል ስለ ልጆችዋ አለቀሰች፥ መጽናናትም አልወደደችም፥ የሉምና የተባለው ተፈጸመ"(ማቴ፤ 2፡16-18)። እንዲሁም ከክፋት እንዲመለሱ የገሰጻቸውን ጻድቅ ባኀታዊ፣ የበረሀ ኮከብ፣ የጌታ ባለሟል፣ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስን በግፍ አንገቱን ያስመተሩ ልበ ደንዳኖች ናቸው። "እርስዋም በእናትዋ ተመክራ የመጥምቁን የዮሐንስን ራስ በዚህ በወጭት ስጠኝ አለችው። ነገር ግን ስለ መሐላው ከእርሱም ጋር ተቀምጠው ስላሉት ሰዎች እንዲሰጡአት አዘዘ፤ ልኮም የዮሐንስን ራስ በወህኒ አስቆረጠው። ራሱንም በወጭት አምጥተው ለብላቴናይቱ ሰጡአት፥ ወደ እናትዋም ወሰደችው" (ማቴ፤ 14፡9-11)። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ምስላችን ተጠርቦ በአደባባይ ቆሞ እንመለክ አላሉም።



**የሮማ ቄሳሮች፤** በተለይም ከክርስትና መሰበክ ዋዜማ እስከ 300 ዓ.ም. አካባቢ ድረስ የተነሱት ቄሳሮች ግን ከላይ የተጠቀሱት ነገሥታት ሁሉ የሠሩትን በደልና ግፍ አብዝተው የፈጸሙ እጅግ በጣም ግፈኞች ነበሩ። ከምንም በላይ ሰይጣን አምልኩኝ ብሎ እንደተጣለ ለመነሳትም ከቶ ምክንያት እንዳላገኘ እንዲሁ ቄሳሮችም ከአርዕስተ ኃጣውእ አንዱና ዋናው በሚሆን በትዕቢት የተነደፉ፣ ራስን በማምለክ አባዜ ናላቸው የዞረ በመሆኑ ምክንያት ምስላቸውን አስጠርበው በሮማ ዋና ዋና አደባባዮች አስቁመው እንዲያመልኳቸው አድርገው ነበር። በዚህም ጊዜ ፍጥረታትን ሁሉ ፈጥሮ የሚገዛ ልዑል እግዚአብሔርን ከሚያመልኩ ጥቂት ክርስቲያኖች በቀር ለሆዳቸው ያደሩ፣ ይገድሉናል ብለው ለሥጋቸው የፈሩ አያሌ ሮማውያን ለጣዖታቱ ሽቱ እየነሰነሱ፣ በግንባራቸው እየተደፉ ይሰግዱ ነበር። ይህ ተግባርም አምልኮተ ቄሳር **(Caesar Worship)** እየተባለ ይጠራል።

ዛሬም አምልኮተ እግዚአብሔርን ለማስፋፋት፣ ክርስቶስ በደሙ የዋጃትን ቤተክርስቲያን ለመጠበቅ የተቀበሉትን ታላቅ ኃላፊነት የዘነጉና ከመንጋው ይልቅ ለራሳቸው የሚሳሱ አባቶች ይህን ቄሳራዊ ተግባር ሲከተሉት በዓይናችን ተመለከትን፤ ይልቁንም በቅድስት ቤተክርስቲያን ቅጽረ ግቢ ውስጥ ሲደረግ ማየታችን እጅግ አድርጎ ያሳዝናል። ስለዚህም ከተጠሩለት ታላቅ የክህነት ተልእኮ ይልቅ ያልተጠሩበትን ግብረ ነገሥታት ዓላውያን በመከተልዎ "ብፁእ ወቅዱስ" የሚለውን ከመጠሪያ ስምዎ ቀድሞ የሚነገረውንና የሚጻፈውን ታላቅ የቅድስና ስም በሥራዎ ስለተቃረኑትና እንደ ሮማ ሮማቄሳሮች የራስዎን ምስል በማስቆምዎ ምክንያት ባስጠረቡት ጣዖት አንጻር "ጳውሎስ ቄሳር" ብሎ ለመጥራት እንገደዳለን።

አዎን! "የመልክ ክፉ በስም ይደግፉ" እንዲሉ ምናልባት መጠን ያለፈውን ግፍና ጣራ የዘለለውን ራስን የማምለክ አባዜ ይሸፍን ይሆናል ተብሎ ጥሩ የተባለው ስም ሁሉ በወረንጦ እየተለቀመ፣ በአዋቂ እየተቀመመ በመጠሪያ ስምዎ ፊትና ኋላ ቢደረደር እንደታሰበው መልካምነትን ሊያመጣልዎ አልቻለም። "እስመ ስሙ ይመርሖ ኀበ ግብሩ" እንደተባለው ወይ እየተመረጠ የተሰጠዎ መልካም ስም መርቶ ከመልካም ሥራ አልደረሰዎትም። እንዲያውም ይባስ ብሎ በብቃትና በችሎታ ሳይሆን በሥጋ ዝምድናና በጥቅማጥም የከበቡዎት "ሆድ አደር" አሽቃባጮች በብዙ ድካም አስጠንተው የሚደርቡልዎትን የስም ጋጋታ እየጣሰ ግፉና ተንኮሉ ብቅ እያለ በጣም አስቸገራቸው። ይህንኑ ግፍዎን ለመሸፈንና ቅድስናዎን ከሰማይ በላይ ከፍ ለማድረግ ሎሌዎችዎ በአፍም፣ በመጽሐፍም፣ አልፎ ተርፎ ጣዖት (ሐውልት) በማቆም ያለእረፍት መባዘናቸው ቢያሳዝነኝ ከግብርዎ ጋር የሚሄደውን፣ ከላይ ከጠቀስኳቸው ጥንታውያን ነገሥታት ጋር የሚያስተካክልዎትን ትክክለኛ ስምዎን ልነግራቸው ወደድኩ። እነሱስ ለምን አጉል ይድከሙ።

ለእርስዎም ሆነ እጅግ አድርገው ለሚያስቡልዎት ወዳጆችዎ የቀደሙ ብፁአን አበው ሲጠሩበት የኖሩት **"ብፁእ ወቅዱስ"** የሚለው የቅድስና መጠሪያ አላረካችሁም፣ **"ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት"** የሚለው ማዕርግ በቂ መስሎ አልታያችሁም፣ **"ፓትርያርክ"** የሚለው አጠራርም በእናንተ ዘንድ በቂ አልሆነም። ስለዚህ **"ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም"** ከዚያም ወደ መሐል መጥቶ **"ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት"** የሚሉት ስሞች ተደረቡልዎ። አሁንም አልበቃዎ፣ ወዳጆችዎም ለቅዱስ አባታቸው ሌላ ስም ከመፈለግ አላቆሙም። የቤተክርስቲያኑ የቅድስና ስም በአምስት አጠፌታ (በድርብ፣ በድርብ) ተሞከረ፣ አልበቃችሁ ሲል ወደ ዓለም ብቅ አሉና ንጉሥ (ፕሬዚደንት) የሚለው ስም ደግሞ አማረዎ። ስለዚህ ወዳጆችዎ ለዚሁ ተግባር ታጥቀው የሚሠሩ የበቁና የነቁ ናቸውና **"የዓለም…..ፕረዚደንት"** እና **"የዓለም…..የክብር ፕሬዚደንት"** የሚሉ ስሞችን ስላገኙልዎ እርስዎም ተረጋግተው ወደ ሥራዎ ያተኩራሉ፣ ድካም የበዛባቸው ወዳጆችዎም ጥቂት እረፍት ያደርጋሉ ብለን ተስፋ አድርገን ነበር። ነገር ግን እረፍት የለም። በፍጹም።

ለስምና ለዝና ይህን ያህል ሲደከሙና ሰውም ሲያደክሙ፤ በተለይም ስምዎን እንደ ንግድ ፈቃድ ለጥፈው ያለሕግ በሚመዘብሩት የቤተክርስቲያን ገንዘብ ዓይናቸው ታውሮ ከአፍዎ የወጣውን ቃል ቀርቶ አያውቁትም እንጂ በልብዎ የሚያስቡትን ሁሉ ለመፈጸም የሚዳዳቸው ሎሌዎችዎ ጥሩ ስም ለማግኘት መንገላታታቸው ስለተሰማኝ የሚስማማ ስም ከነ ማብራሪያው እነሆ።

- እንደ ፈርዖን "አላውቅም፣ አልለቅም" በሚል ጭፍን ጉዞ ቤተክርስቲያንን ስለከፋፈሉ፣ እንደ ሔሮድስ ሕጻናት በግፍ ሲገደሉ የሚቾቹን ቤተሰቦች በማጽናናት ፋንታ ከገዳዮች ጎን ቆመው የማስፈራሪያ ፉከራ

በማሰማትዎ፣ ደግሞም የጣሱትን ሕገ ቤተክርስቲያን ያክብሩ ይመለሱ እያሉ የሚመክሩዎትን የክህነትና የክርስትና ወንድሞችዎ የሚሆኑ ብፁአን ሊቃነ ጳጳሳትን በግፍ በማስደብደብዎ፣

- እንደ ናቡከደነፆር ወርደ ሠፊ በሆነ ሰሌዳ ላይ የራስዎን መልክ አሠርተው በየአብያተክርስቲያናቱ በማቆምዎ፣ በቅድስት ቤተክርስቲያን ላይ፣ እንደ ዓይን ብሌን በምታያቸው ሊቃውንት ላይ እንዲሁም መተኪያ በሌላቸው ንዋያተ ቅድሳት ላይ ግፍ እየሠሩ ስለሚገኙ፣



አሁን ደግሞ ይባስ ብለው እንደ ቄሳር ሐውልትዎን አስጠርበው በቅጽረ ቤተክርስቲያን ምእመናን አምልኮትና ስግደት በሚፈጽሙበት አንጻር (አቅጣጫ) አስቁመው እንዲሰገድልዎ (እንዲመለኩ) በማድረግዎ፤

ጥሩ ስም ፍለጋ ታማኝ ሎሌዎችዎ ያለ እረፍት በጣም ከሚደክሙ በግብር ከሚመስሏቸው ኃያላን ከነገሥታ ጋር በስም እንዲተካከሉልን **አባ "<u>ጳውሎስ ቄሳር</u>"** *ወፈርዖን ወናቡከደነፆር ወሔሮድስ* የሚለውን ስም እነሆ። ከዚህ በኋላ ለስም ፍለጋ እንደማይማስኑ ተስፋ አለን።

ከታሪክ እንደምንረዳው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ አቡነ ሰላማ የወንጌል ብርሃን በምድረ ኢትዮጵያ እንዲበራ ስላደረገው ከፍ ያለ ሐዋርያዊ ትሩፋት ሕዝቡ "ከሳቴ ብርሃን" ብሎ ጠርቶታል። እኛም የራስዎን መልክ አሠርተው፣ አሁን ደግሞ ምስልዎን አስጠርበው በቅጽረ ቤተክርስቲያን አስቁመው በአንጻርዎ እንድንሰግድ ስለፈለጉ ከሮማ ቄሳሮች ጋር በሚያመሳስልዎ ሥራዎ ምክንያት ሕዝቡ ስለ ቄሳራዊ ተግባርዎ "ጳውሎስ ቄሳር" ብሎ ቢጠራዎ ተገቢ ነው።

የሚገርመው ነገር ከላይ ከፍ ብለን ከጠቀስናቸው ግብዝ የሮማ ነገሥታት መካከልም ቢሆን ትዕቢታቸው በክርስትናው የፍቅር ክንድ ተሰብሮ ራሳቸውን ከማምለክና ከማስመለክ ይልቅ ክርስቶስን ማምለክ የመረጡ እንደ ጢባርዮስ ቄሳር ኋላም እንደ ታላቁ ቆስጠንጢኖስ ያሉ ነገሥታት ነበሩ። ክርስትናው በመላው ዓለም በተለይም በወቅቱ የሮማ ግዛት (Roman Empire) እየተባለ በሚጠራው ሠፊ ግዛት እየተስፋፋና እየተጠናከረ ሲመጣ ቀድሞ ነገሥታቱ ለአምልኮተ ጣዖት ይጠቀሙበት የነበረው ቅርጻ ቅርጽ ሥነ ጥበብ ወደ ቤተክርስቲያን ሰርጐ ገብቶ በተለይም በሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን የጌታ፣ የእመቤታችን፣ የመላእክት፣ የጻድቃን፣ የሰማዕታት ምስል እየቀረጹ መጠቀም ጀመሩ። ይህም ሆኖ ቅርጻ ቅርጽን (Images) ለቤተክርስቲያን አገልግሎት ማዋል የምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት (በተለይም የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን) ልማድ ወይም ባህል ሆኖ ቆዬ እንጂ በምሥራቅ አብያተክርስቲያናት በተለይም በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ጨምሮ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ባለ ሁለት ወርድ Two-dimensional (2D) በሆነ ሰሌዳ/ግድግዳ ላይ የሚሳሉ ሥዕላትን እንጂ ባለ ሦስት ወርድ Three-dimensional (3D) በሆኑ ቁሳቁስ የሚሠሩ ቅርጻ ቅርጽን አይቀበሉም። ይህም የሆነበት ምክንያት ቅርጻ ቅርጽ (Images) የምዕራባውያንን የአምልኮ ጣዖት ቅሪት የሚያስታውስ ስለሆነ፣ እንዲሁም 2D ሥዕላት ውክልናቸው ሐሳባዊ (መንፈሳዊ) ሲሆን 3D ቅርጻ ቅርጽ ግን ንጽጽራዊነትን የሚያስከትል በመሆኑ ነው።

በዚሁ ምክንያት በእኛም ቤተክርስቲያን አልፎ አልፎ በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል፣ በታዕካ ነገሥት በዓታ ለማርያም፣ በደብረ ሰላም ቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ቅጽረ ግቢ ውስጥ የሚገኙ የጌታ፣ የእመቤታችን፣ የሐዋርያት ቅርጾች/ምስሎች በተለያዩ ጊዜያት የውዝግብና የልዩነት ምክንያት ሆነው መቆየታቸውና አሁንም ልዩነቱና ትችቱ ያልተፈታ ሆኖ እንዳለ ከዚህ በፊት ብዙ ጊዜ ተወስቷል።

**አባ "ጳውሎስ ቄሳር" ሆይ፦**
ይህን የምዕራባውያንን የአምልኮ ጣዖት ቅሪት፣ በዚያውም ላይ ከራስዎና ከጥቂት "ሆድ አደር" ሎሌዎችዎ በስተቀር ሌላው የማይቀበለውን ይህን የምስል (ጣዖት) ቀረጻ ማስፈጸምዎ፣ በተለይም ጣዖቱ በቅጽረ ቤተክርስቲያን እንዲቆም ማድረግዎ፤ ከዚህ ቀደም ከሁለት የላቲን አገሮች ከተበረከቱልዎ ኒሻኖች ጋር

በቫቲካን ቤተክህነት የተሰጠዎትን ስውር ካቶሊካዊ የብረዛ ተልዕኮ ያለተከላካይ በገሃድ እያጧጧፉ መሆኑን ፍንትው አድርጐ የሚያሳይ ተግባር ነው።

እርግጥ ነው፦ በቅድስናቸውና በመልካም ሥራቸው የሚከበሩና የሚፈቀሩ፣ በሕይወት ዘመናቸው የፈጸሙት ገድልና የሠሩት ትሩፋት በዘመኑ ለሚኖረው ትውልድ ብቻ ሳይሆን ኋላ ለሚነሳው ትውልድ ሁሉ አርአያ ሊሆን የሚችል ደጋግ አባቶች በሞት ሲለዩ የሠሩት መልካም ሥራ አብሮ እንዳይቀበር መልካም ሥራቸውን የሚያስታውስ ልዩ ልዩ መታሰቢያ ይደረግላቸዋል፤ መልካም ሥራ በፈጸሙበት ሥፍራ ወይም በመቃብራቸው ላይ ሐውልት እንዲቆምላቸው ይደረጋል።

ከታሪክ አንጻርም ለሀገራቸው ሉዓላዊነት፣ ለሕዝባቸው ነጻነት የሚያኮራ ተጋድሎ የፈጸሙ ጀግኖች አርበኞች፣ በተሰለፉበት መስክ ያለ እረፍት በመሥራት በመልካም የሥራ ፍሬያቸው የትውልድን አዕምሮ የሚቃኙ ታላላቅ ሊቃውንት ዓረፍተ ዘመን ገትቷቸው መጻኢው ትውልድ በአካል ሊያገኛቸው ባይችልም እንኳ በመታሰቢያቸው መነጽርነት ወደ ኋላ መለስ ብሎ ታሪካቸውን በማውሳት በበጐ ሥራቸው እንዲነቃቃና እርሱም በተራው ለበጐ ሥራ እንዲታትር የሚያደርግ መታሰቢያ ይደረግላቸዋል። ይልቁንም መልካም የሥራ ፍሬ ባሳዩበት ወይም አጽማቸው ባረፈበት ሥፍራ የመታሰቢያ ሐልት ይቆምላቸዋል።

ለምሳሌም፦ ለኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖታቸውና ለኢትዮጵያ ሀገራቸው ሲሉ በፋሺስቶች ተገድለው ሰማእት ለሆኑት ብፁአን አበው አቡነ ጴጥሮስ በአዲስ አበባ፣ አቡነ ሚካኤል በጐሬ፣ ለመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ ብፁእ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በደብረ ጽጌ፣ ሃይማኖት የለሽ በሆኑ ጨካኞች እጅ ሕይወታቸው ላለፈው ለሁለተኛው ፓትርያርክ ለሰማዕቱ ብፁእ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በጐፋ፣ መምለኬ እግዚአብሔር በሆነች ሀገራችን ላይ ፀረ ሃይማኖት ርዕዮተ-ዓለም ሠፍኖ በነበረበት ታላቅ የፈተና ወቅት ቤተክርስቲያናቸውን ለታደጉት ሦስተኛው ፓትርያርክ ብፁእ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሥላሴ አጽማቸው ባረፈበት ወይም ተጋድሎ ባደረጉበት ቦታ ላይ ተሠርቶላቸዋል። እነዚህ ሁሉ የሕይወት ዘመናቸውን በመንፈሳዊ ተጋድሎና በትሩፋት የፈጸሙ አባቶች በመሆናቸው በሞተ ሥጋ ቢለዩም የሠሩት መልካም ሥራ በሕዝበ ክርስቲያን ዘንድ የሚወደድ በመሆኑ ከሞቱ በኋላ ለማይሞተው ሥራቸው መታሰቢያ ተደርጎላቸዋል። ይኸውም ቢሆን መልካም ሥራ በሠሩበት ቦታና አጽማቸው ባረፈበት ሥፍራ እንጂ አምልኮትን በሚቃረን መልኩ በቅጽረ ቤተክርስቲያን አይደለም።

በሰሞኑ በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ቅጽረ ግቢ ውስጥ የቆመው ሐውልትዎ ግን በሮማ ቄሳሮች ዘመን እንደተደረገው ራስን አለቅጥ መውደድና ማክበር ከተጠናወተው እከብር ባይ ልቡና የመነጨ፣ በጥቂት “ሆድ አደር” ሎሌዎችዎ የተቀነባበረ፣ መንፈሳዊም ሆነ ሞራላዊ ምክንያት የሌለው ኢ-ክርስቲያናዊ ተግባር ነው። ሐውልት በአደባባይ ይቆምልዎ ዘንድ እንደ ብፁአን አበው አቡነ ጴጥሮስ፣ አቡነ ሚካኤልና አቡነ ቴዎፍሎስ በግፈኞች እጅ መሞቱ ይቅርብዎና ለሥልጣን ሲሉ የንጹሐንን ደም በአደባባይ ያፈሰሱ እብሪተኞችን በመደገፍ ወገኖቻቸው ግንባራቸውን በጥይት እየመቱ በየሜዳው የወደቁባቸውን ሐዘንተኞች በሚድያ ማስፈራራቱን በተው፣ ለእግራቸው ጫማ ሳይኖራቸው፣ ደመወዝ የሚባል ነገር ሳያውቁ በፍጹም ብኅትውና እንደኖሩት እንደ ሦስተኛው ፓትርያርክ ብፁእ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት መሆኑ ይቅርና በድሃዋ ቤተክርስቲያን አቅም ከአንድም ሁለት ጊዜ በሚልዮን በሚቆጠር ገንዘብ ጥይት የማይበሳው መኪና እየገዙ መንፈላሰሱን ባቆሙ ነበር። ስለሆነም ቄሳራዊ ሐውልትዎ ክርስቶስ በሚመለክበት፣ የመስቀሉ ላይ ልዩ ፍቅሩ በተገለጠበት፣ ለእርሱም በእውነትና በመንፈስ የሚሰግዱለት ሕዝቡ ለጸሎት በሚሰበሰቡበት ታላቅ የቅድስና አደባባይ መቆሙ ወንጌላዊው ማቴዎስ “እንግዲህ በነቢዩ በዳንኤል የተባለውን የጥፋትን ርኩሰት በተቀደሰችው ሥፍራ ቆሞ ስታዩ፥ አንባቢው ያስተውል” (ማቴ፤ 24፡ 15) ሲል የተናገረው ቃል የደረሰበት ፍጻሜ ዘመን መሆኑን የሚያሳይ ነው።

እንግዲህ የትኛው ቅድስና ነው የሚሰገድለት፣ የትኛው ደግነት ነው ዜና መዋዕል የሚጻፍለት ወይስ ሐውልት የሚቆምለት። ምናልባት በዚህ ዘመን ሁሉ ነገር ስለተገለባበጠ ከመገፋት ይልቅ መግፋት፣ ከመሞት ይልቅ መግደል፣ ከትሕትና ይልቅ እምቢተኝነትና ጀብደኝነት ለቅድስና የሚያበቃ ከሆነ አይደለም አንድ ሐውልት ሌላም ሊያደርጉ ይችላሉ። ነገር ግን ያም ቢሆን በቅጽረ ቤተክርስቲያን አይደለም። ሌላው ደግሞ በጐ ሥራ አለኝ ብለው የሚያምኑ ቢሆኑ እንኳን እርስዎ ራስዎ ስለራስዎ እየመሰከሩ አይደለም፣ ካለፉ በኋላ በበጐ ሥራዎ የተማረከው ሕዝብ ደግነትዎን ሲመሰክር እንደ ቤተክርስቲያናችን ሥርዓት ቅዱስ ሲኖዶስ ሲፈቅድ ሐውልቱ ቢቆምልዎ በተሻለ ነበር። ነገር ግን እርስዎ በአካል እያሉ ከአካልዎ በላይ ሐውልት በጐነቴን ይገልጻል ብለው ማመንዎ የሚገርም ነው።

ሐውልቱን ለማሠራት ደፋ ቀና ያሉ ሎሌዎችዎም ቢሆኑ ለጊዜው እርስዎ ሳሉ የሚያሾም የሚያሽልም ሥራ መሥራታቸውንና የሚሹትን ደመወዝ መቀበላቸውን እንጂ ስለ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን፣ ወደፊትም ስለሚሆነው ነገር የሚያስብ አዕምሮ አልታደሉምና ግድ የላቸውም።

በገሃድ ከሚታየው ግፍ በላይ የቅድስናዎን ሰንደቅ ዓላማ ከፍ አድርገው ለማውለብለብ ዓይናቸውን ጨፍነው የተሰለፉት ሎሌዎችዎ በሥራ የማይታይ ፍቅርዎን ወደ ሰው ልብ የሚያስገቡበት የመርፌ ቀዳዳ ያህል ጭላንጭል ቢያጡ፣ ቢጨንቃቸው **"ወደ ልብ ባይደርሱ፣ በደረት ላይ ይፍሰሱ"** ብለው ይቺኑ የፈረደባት ቤተክርስቲያን አራቁተው በውድ ዋጋ መልክዎን በካኒቴራ ላይ አሳትመው በፈረደባቸው ካህናት ላይ ኮታ ጥለው ሲያስሸጡ እንደነበር አይዘነጉትም ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። እንዲያውም ከነምልክቱ አልሸጥ ያለውን በእያንዳንዱ ካህን ኪሳራ ከደመወዙ እየቆረጡ አንቀው እያስከፈሉ ሲመዘብሩ ትዝ አይልዎትም? በዚህ ፈጠራ "ሆድ አደር" ሎሌዎችዎ ሥዕልዎ በሁሉ ደረት ላይ ቦግ ብሎ ይታያል የሚል ተስፋ ነበራቸው። ነገር ግን ከጥቂት "እንወደድ ባዮች" በቀር ወድቀህ ተነሳ ያለውም አለመገኘቱ ሳያሳዝናችሁ እንዳልቀረ እርግጠኛ ነኝ።

ቅድስናዎን ከፍ ለማድረግ ሌት ተቀን መሥራት የማይታክታቸው ታማኞችዎ ሌላ ያስኬዳል ያሉትን ዘዴ ሲያሰላስሉ ቆይተው ያለ ጽርአት ተንበርክከው ሲጸልዩ የሚያሳዩ ትልልቅ ሥዕሎች እንደተለመደው በፈረደባት ምስኪን ቤተክርስቲያን ገንዘብ እጅግ በጣም ውድ በሆነ ዋጋ አሠርተው በየአብያተክርስቲያኑ ማስቀማቸውን ዘነጋሁት እንዳይሉኝ ሥዕሎቹ ከጠቅላይ ቤተክህነቱ ግቢ ጀምሮ በታላቅ አድባራትና ገዳማት በሚታይ ቦታ ከፍ ብለው ስለተሰቀሉ መዘንጋት የማይቻል ነገር ነው። ይባስ ብሎ "ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ" እንዲሉ እየመዘበሩና እያስመዘበሩ የሚያስርቡትን ሕዝብ "ለተራበ እንጀራ፣ ለተጠማ ውሃ…." በዘርና በጐሣ እያናቆሩ የሚያጋጩትን ሕዝብ "ሰላምን ስጥልን…." ምናምን፣ ምናምን እያሉ የተመጻደቁበትን የምጸት ቃል በየሥዕሉ ግርጌ በትልቁ አጽፈው በቤተመቅደሱና በሕዝበ ክርስቲያኑ መተያያ መሐል ላይ መደንቀርዎ ምናልባት ያለውድ በግድ በኔ ሥዕል አንጻር ለማሰገድ ካደረብዎ ግብዝ ቁሳራዊ አመለካከት ነው እንጂ የጸሎት ፍቅር ነው ለማለት ያስቸግራል። አባቶቻችን ጌታ በወንጌል "ስትጸልዩም እንደ ግብዞች አትሁኑ፤ ለሰው ይታዩ ዘንድ በምኩራብና በመንገድ ማዕዘን ቆመው መጸለይን ይወዳሉና፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። አንተ ግን ስትጸልይ፥ ወደ እልፍኝህ ግባ መዝጊያህንም ዘግተህ በስውር ላለው አባትህ ጸልይ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል" (**ማቴ፤** 5፡ 6) ሲል ያስተማረውን ተከትለው ሳይመጻደቁ አማናዊውን (ኦሪጅናሉን) የግል ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ሲያቀርቡ በሚታይባት ቤተክርስቲያን "የጸሎት ቅጅ (ፎቶ ኮፒ)" በሥዕል "እዩልኝ፣ ስሙልኝ፣ ጸሎተኛ ነኝ" ዓይነት ዓዋጅ ከፍ አድርገው ማሳየትዎ ከአይሁድ ጋር አያመሳስልዎትም ይላሉ? እንዴ! ከአይሁድም ባሱ እንጂ! አይሁድማ ጸሎቱን በአደባባይ እያደረጉ ተመጻደቁ እንጂ የጸሎቱን ቅጅ (ኮፒ) በሥዕል አድርገው አልሰቀሉም።

በሀገሪቱ ላይ የተከሰተው የፖለቲካና የመንግሥት አስተዳደር ለውጥ ዕድሉን ከፍቶልዎት የተቆናጠጡትን፣ አሁንም ድንገት ድል እንደቀናው ፈሪ የጦር ጀነራል በብዙ የጦር መሣሪያ አጀብ የተቀመጡበትን መንበር ለማደላደል ሲሉ የፈጸሙትን ግፍ ሁሉ ለመዘርዘር ጊዜም፣ ቀለምም፣ ብራናም አይበቃም። ምናልባት ጥቂት "ሆድ አደር" ሎሌዎችዎ በየዕለቱ ተግተው በጆሮዎ እንደ ጅረት በሚያፈሱልዎ በጥቅም የተቃኘ የ"ቅዱስ አባታችን" የምጸት የሰላምታ የፈጸሙትንና ያስፈጸሙትን ሁሉ ሊያስረሳዎ ይችል ይሆናል። እንዲህ ያለው ችግር እውነተኞች በድፍረት የሚነግሯቸውን እርምት ከመስማት ይልቅ ደካሞች በፍርሐት፣ ኅሊና ቢሶች በብልጠት ተሞልተው ዘወትር የሚያወርዱላቸውን መወድስ ብቻ መስማት በሚፈልጉ ዘንድ የተለመደ ነውና አይፈረድብዎትም።

ከብዙ በጥቂቱ፣ ከሙሉ በከፊሉ አለፍ አለፍ እያልኩ እስኪ ላስታውስዎ።

1. የሃይማኖትና የክህነት ወንድሞችዎን፣ ፓትርያርክን ጨምሮ ብፁአን አባቶች ሊቃነ ጳጳሳትን በወዳጆችዎ ጠመንጃ አፈሙዝ አሳድደው፣ ቤተክርስቲያን በሁለት ሲኖዶስ ተከፍላ መከራዋን እንድታይ ምክንያት መሆንዎን ለአፍታ እንኳ አስበውት ያውቁ ይሆን? አስበውት የሚያውቁ ከሆነ ምን ይሰማዎት ይሆን? ቤተክርስቲያን በሁለት ሲኖዶስ እንደተከፈለች፣ በተለይም በውጭ ያለችው ቤተክርስቲያን በሦስትዮሽ የአስተዳደር ረድፍ (አዲስ አበባ፣ አሜሪካ እና መሐል ሠፋሪ) ተከፋፍላ፣ በልዩነትና በጥላቻ እንደ ብራና ተወጥራ በመበጣጠስ አፋፍ ላይ ሳለች ዓይንዎን ጨፍነው፣ ጆሮዎን ደፍነው፣ "አላየሁም፣ አልሰማሁም" ብለው ሲኖሩ ሰው ነዎትና በመሐል ቢጠሩ በጎ ይመስልዎታል? እርግጥ ነው የሰላም መልእክተኞች ልኬያለሁ ሊሉ ይችሉ ይሆናል። ለመሆኑ ለይስሙላ መልእክተኛ ከመላክ ይልቅ መጀመሪያ ከራስዎ ጋር

ኋላም በአጠገብዎ ከሚገኙ ብፁአን አባቶች ጋር ሰላም ቢፈጥሩ፣ "ሕገ ቤተክርስቲያን ይከበር" ሲሉዎት ማስደብደቡን፣ ማስፈራራቱን ቢተው ምናለ። ሰላም መልካም ልብ የሚመነጭ የኅሊና ሚዛን እንጂ ለይስሙላ መልእክተኞች በመላክ ለሚድያ ፍጆታ የሚያውሉት ፖለቲካዊ ድርድር አይደለም።

2. በአገዛዝዎ ሥር የወደቀችውን የአገር ቤቷን ቤተክርስቲያን (ስም መጥቀስ ባያስፈልግም) እነማን ናቸው በፈላጭ ቆራጭነት የሚያዙባት፣ የሚናዝዙባት? በክርስትናው ወንድሞችዎ በክህነት እኩዮችዎ የሚሆኑ ቀና ብሎ በሙሉ ዓይን ለማየት እንኳ የሚፈሩና የሚታፈሩ ብፁአን ሊቃነ ጳጳሳትን ሥልጣንዎን ተገን ያደረጉ የሴት ወይዘሮዎች "አንተ" እያሉ ከፍ ዝቅ አድርገው እንደሚዘልፉና እንደሚያዋርዱ አላውቅም ይሉኝ ይሆን? መስማትዎን እንኳን አልጠራጠርም። ነገር ግን  "እኔን ቅዱስ አባታችን ካሉ ይበቃል" ብለው ከሆነ ተሳስተዋል። ጊዜውን ጠብቆ ተባርዮ ለማንም አይቀርም። ዛሬ ካልታረመ ነገም ጥቅሙ ሲነካበት፣ ክብሩ ሲቀርበት ወደ ኋዳዎ ብቅ ማለቱ አይቀሬ ነው።

3. እውነትን ስለተናገሩዎ፣ "ቅዱስ" እያሉ ስላልሸነገሉዎ፣ በተንኮል የተገደሉ፣ ከሥራ የተባረሩ፣ በረሀብና በጥም እየተሰቃዩ ያለፉ ስንቶች ናቸው? በክርስትና ሕግ በሚመራ የሃይማኖት ቤት ቀርቶ ሰብአዊ መብትን በሚያከብር አንድ ተራ መሥሪያ ቤት እንኳን የማይደረግ ግፍ እየተፈጸመባቸው፣ የአንድ ጐልማሳ ዕድሜ ለሚያህል ዘመን ካገለገሏት ቤተክርስቲያን ያለ ደመወዝ፣ ያለጡረታ የተባረሩ አባቶችና ወንድሞችን አላውቅም ይሉኝ ይሆን? አላውቅም ካሉ ከእውነት ጋር እየተጣሉ መሆንዎን ኅሊናዎ ይንገርዎ። ኅሊና አይዋሽምና።

4. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ ምናልባት የመጀመሪያ በሚባል ሁኔታ፣ ታቦተ ሕጉ በቆመበት የቅድስና አደባባይ ባሕታዊ በጥይት ተደብድቦ መሞቱን ይዘነጉት ይሆን? እርግጠኛ ነኝ አይዘነጉትም። ግን ምን ይታወቃል ቅድስናዎን ከመጠን በላይ እያበዙ የሚያወድሱዎ ሎሌዎችዎ በጆሮዎ የሚያዘንቡት የምጸት ምስጋና እንዲህ ያለውን እውነት ለመስማትም ሆነ ለማሰብ ጊዜዎን ሊሻማዎ ስለሚችል ዘንግተውት ይሆናል። ደግሞም ሊገድልዎ ሲል ነው የሞተው ብለው የሚሸነግሉዎትን ታማኞችዎን አምነው ይሆናል። ምናልባት ከተዘነጋዎ አንድ ሌላ በዕለቱ ያስደረጉትን ነገር ልጥቀስና ላስታውስዎ። ወዳጆችዎ እንዳቀነባበሩት ሊገድልዎ የተጋበዘ ጠላት ቢሆን እንኳን ከሞት በኋላ "በኔ ምክንያት በተቀደሰው አደባባይ ደም ፈሰሰ፣ ነፍስ ጠፋ" ብሎ በመጸጸት ፋንታ በታላቅ ጀብድ ወደ ቤተመንግሥትዎ ተመልሰው "ሠይፎሙ ይባእ ውስተ ልቦሙ" እያለ ያቅራራልዎትን አድር ብዬ ድምጻዊ ተከትለው ያሰሙትን የጀብደኝነት ፉከራ ያስታውሱታል። ምናልባት ከጊዜው ርዝመት፣ ከውዳሴው ብዛት የተነሳ አሁንም ትዝ ካላለዎ ሌላ ያደረጉትን ነገር ላስታውስዎ። ጻድቃን በገዳም አበውን የረዱበት፣ የጽድቅ ተጋድሎ የፈጸሙበት፣ ሰማዕትነት ተቀብለው የቆሰሉበት/የሞቱበት ዕቃ/ልብስ መታሰቢያ ሆኖ ሲቀመጥ ቢያዩ እርስዎም ለምን ይቅርብኝ ብለው ባሕታዊው በተገደለ ቀን የለበሱትን ልብስ መታሰቢያ ብለው እንዳ አባ ገሪማ ገዳም ቤተ መዘክር እንዲቀመጥ ማድረግዎን መቼም አይዘነጉትም። አላፍር ብለው "ዜና መዋዕል ዘብፁእ ወቅዱስ" ተብሎ በአሽቃባጮችዎ በተጻፈ መጽሐፍዎ ላይ "ሰማዕትነት የተቀበሉበት ልብስ" ተብሎ ተጽፎለታል፣ ሥ ዕሉም ተለጥፏል። ሰማዕትነት መሞት ነው ወይስ መግደል? መሰደድ ነው ማሳደድ?

5. ሰው በሕይወት ሳለ ቢበደል ወይም ቢበድል ሞት ታላቅ ጥሪ ነውና ያስታርቀዋል። እስኪ መለስ ብለን እስከ መቃብር የተበቀሏቸውን፣ በተወለዱባት ሀገር፣ ባደጉባትና ባገለገሉባት ቤተክርስቲያን በነጻነት ሠርቶ የመኖር መብት ማጣታቸው ሳያንሳቸው ኢትዮጵያዊ ይቅርና ማንም በተፈጥሮ ሰው የሆነ ሁሉ የማይከለከለውን የመቃብር አፈር ተከልክለው በሕይወትም በሞትም ግፍ የተቀበሉ አባቶች ስንት ናቸው? እነሱንስ አላውቅም ይሉ ይሆን? ይዘነጓቸው ይሆን? በክርስቲያናዊ በጐነትና በሰብአዊ ርኅራኄ ለነዚህ አባቶችና ወንድሞች ጸሎተ ፍትሐት ያደረጉ፣ ግብአተ መሬት የፈጸሙ ካህናት በእርስዎ ቀጥተኛ ትዕዛዝ፣ በ"ሆድ አደር" ሎሌዎችዎ አስፈጻሚነት ከሥራ መባረራቸውን፣ ከደመወዝ መታገዳቸውን ዘነጋሁት ይሉኝ ይሆን? ዘነጋሁት ቢሉኝ አይደንቀኝም፣ "አውቆ የተኛ ቢቀሰቅሱት አይሰማ" ነውና።

እንዲያው ላስታውስዎ ጥቂቱን አነሳሁ እንጂ በጠቅላላው ለፈተና በተቀመጡባቸው 18 የግፍ ዓመታት ውስጥ የፈጸሙትና ያስፈጸሙትን ሁሉ መዘርዘር አይቻልም። ምን ወረቀት ይችለዋል? በጣም፣ በጣም፣ በጣም ብዙ ነውና።

# የመጨረሻ መልእክት

**“ ማኔ፣ ቴቄል፣ ፋሬስ ” ዳን፤ 5፡ 25**

ማኔ፣ ቴቄል፣ ፋሬስ የሚለው ቃል በተቀደሱት የእግዚአብሔር ንዋያት የማይገባ ሥራ የሠራውን የፋርሱን ንጉሥ ናቡከነፆርን ለማስጠንቀቅ በግብር አምላካዊ፣ በአጽባእተ እግዚአብሔር በእልፍኙ ግድግዳ ላይ ተጽፎ የተገኘ ቃል ነው። እስራኤል እግዚአብሔርን በማሳዘናቸው ምክንያት ለፋርስ ነገሥታት አልፌው ተሰጥተው በነበረበት በዚያ ወቅት ቤተመቅደሱ ተመዝብሮ፣ እነርሱም ሆነ የቤተመቅደሱ ንዋያተ ቅድሳት ተማርከው በባቢሎን ይኖሩ ነበር።

ግብዙ ንጉሥ ናቡከነፆር በንዋያተ ቅድሳቱ ላይ ከሚከብርባቸውና እርሱን ጨምሮ ዓለሙን ሁሉ ፈጥሮ ከሚገዛው ከኃያሉ አምላክ ከልዑል እግዚአብሔር ይልቅ በዙሪያው ሆነው ጠጅ እየቀዱ፣ ጮማ እያወረዱ “ንጉሥ ሆይ ሺህ ዓመት ንገሥ” በሚለው የማታለያ “ነጠላ ዜማቸው” መዋቲ መሆኑን እንዲረሳ እያደነዘዙ ከርሳቸውን የሚሞሉ ሆዳም ተከታዮቹንና አብረውት በኃጢአትየሚወድቁ ዕቁባቶቹን ለማስደሰት ሲል ከ እግዚአብሔር ጋር የሚያጣላውን ሥራ ፈጸመ። ናቡከደነፆር ታላቅነቱን በተከታዮቹ ፊት ለመግለጥ ሲል ቅዱሱ እግዚአብሔርን በቅድስና ይገለገልባቸው ዘንድ የመረጣቸውንና ያከበራቸውን ንዋያተ ቅድሳት የጠጅ መጠጫ፣ የሰው መላገጫ በማድረጉ ምክንያት በፍትሕ አምላካዊ ዘመንህ ተቆረጠ፣ በመድሎተ አምላክ ተመዘንህ ከገለባ ይልቅ ቀልለህ ተገኘህ፣ ክብርህም ለሌላ አልፎ ተሰጠ እንደተባለ ቅዱስ መጽሐፍ ያስተምራል።

አሁንም በዘመናችን በክርስቶስና ደሙን ባፈሰሰላቸው ንፁሐን ሕዝበ ክርስቲያን መካከል በትሕትና እንዲያገለግሉት ከጠራዎና በአባትነት ያከበረዎን አምላክ በትሕትና በማገልገል ፋንታ ድሆች ለፅድቅ ብለው ከራሳቸውና ከልጆቻቸው ጉሮሮ እየነጠቁ ለቤተክርስቲያን በሚመጸውቱት የእንባ ገንዘብ ብዙ ሚልዮን ብር የሚያወጣ ጥይት የማይበሳው መኪና መግዛትዎ (ማስገዛትዎ)፣ ሥዕልዎን በውድ ዋጋ አሠርተው በየአብያተክርስቲያኑ ማስቀምዎ አንሶ ክርስቶስ በደሙ ዋጅቶ ለቅድስና ተግባር በመረጣትና ባከበራት በተቀደሰችው የእግዚአብሔር አደባባይ ቄሳራዊ ሐውልትዎን በማቆምዎ ና እግዚአብሔር በደሙ በቀደሳቸው ካህናትና ንዋየ ቅድሳት ተጠቅመው ይህንኑ ቄሳራዊ ሐውልት መመረቅዎ ለአሕዛቡ ንጉሥ ለናቡከደነፆር የተላለፌው ማኔ፣ ቴቄል፣ ፋሬስ የሚለው መልእክት ይመለከትዎታል።

ይቺን ቤተክርስቲያን ለብዙ ዘመናት ያህል ታግለዋታል፣ ፈጽመው የተቆጣጠሯት መስሎዎት ይሆናል። ምናልባትም ለጥቂት ጊዜያት ተቆጣጥረዋታል፣ የወደዱትን ፈጽመውባታል፣ አስፈጽመውባታል። ነገር ግን ሰው ነዎትና ለዘላለም አይኖሩም። እርሷ ግን የተመሠረተችው በህያው አምላክ በክርስቶስ ደም ስለሆነ ለዘላለም ጸንታ ትኖራለች። በሚያልፍ ጥቂት ዘመን የማያልፍ ጠባሳ ጥሎ መሄድ በእግዚአብሔር ዘንድ ያስጠይቃል፤ በታሪክ ና በትውልድም ያስወቅሳልና ይህን ለማረም መፍትሔው በእጅዎ ነው።

ለዚች በዘመናት ለከበረች ነገር ግን ሕዝቧን ልትመሩ በተሾማችሁ አባቶች ምክንያት ጀማሪዎች በሚሳለቁባት ምስኪን ቤተክርስቲያን የእርስዎ ጥይት የማይበሳው መኪና፣ በውዳሴ ከንቱ የዳጎሰ ዜና መዋዕል፣ በኀብረ ቀለማት ያሸበረቀ ሥዕል፣ ከነሐስም ይሁን ከድንጋይ የተጠረበ ሐውልት “በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ” መሆኑን ይገንዘቡ። ለዚች በሰላም እጦት ለምትታወክ ቤተክርስቲያን በአካለ ሥጋ አድርገውት የማያውቁትን ከመጠን በላይ ተንጠራርተው ሲባርኩ የሚያሳይ የድንግጋይ ሐውልት ማሠራት ጉዳት እንጂ ጥቅም የለውም። ከዚህ ይልቅ በትሕትና መንፈስ ለእውነተኛ ለእርቅ ተዘጋጅቶ ለአንዲቷ ቤተክርስቲያን የፍቅርና የሰላም የአንድነት ሐውልት መሥራት ይሻላልና አሁን በቅርብ ጊዜ ያስጠረቡትንና በቦሌ መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ግቢ ያቆሙትን ኢ-ቀኖናዊ ሐውልት (ጣዖት) አፍርሰው የፍቅርና የሰላም ሐውልት ለማቆም እንዲችሉ አምላክ ያመልክትዎ።

**ቃለ-አብ**
**ከለንደን**